# የታዳኝ ዱር እንስሳት ቆጠራና ኮታ አሰጣጥ መመሪያ

# ቁጥር 853/2014

## የታዳኝ ዱር እንስሳት ቆጠራና ኮታ

## አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 853/2014

የዱር እንስሳት ሃብት ባልተቀናጀና አግባብነት በሌለው አጠቃቀም ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነና ለአደጋ ተጋላጭነቱ እየጨመረ በመምጣቱ፤

የዱር እንስሳት አጠቃቀም የዱር እንስሳቱን አደጋ ላይ የማይጥልና ህጋዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የዱር እንስሳት በፍጆታዊ የአጠቃቀም ስልት አማካይነት ከዱር እንስሳት ሃብት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በማጎልበት ለሀገሪቱ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በታዳኝ ዱር እንስሳት ቆጠራና የኮታ አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ የአሠራር ክፍተቶችን በማስወገድ ወጥነት፣ ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነት የሰፈነበት የአሠራር ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ቀደም ሲል የወጡትን የዱር እንስሳት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 እና የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2001 ማስፈጸሚያ መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/1999 አንቀጽ 17 (2) በተደነገገው መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የታዳኝ ዱር እንስሳት ቆጠራና ኮታ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 853/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

1. **"አዋጅ"** ማለት የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/199 ነው፤
2. **"ደንብ"** ማለት የዱር እንስሳት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ደንብ ቁጥር 163/2001 ነው፤
3. በአዋጁ እና ደንቡ አንቀጽ 2 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤
4. **"የዱር እንስሳት ቆጠራ"** ማለት ዱር እንስሳት ሥነምህዳራዊና ሥነ ህይወታዊ ሁኔታ (ሥርዓተ ተዋልዶ፣ የፆታና ዝርያ ስብጥር፣ የመኖሪያ አካባቢ) በሚመለከት ሳይንሳዊ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ የታዳኝ የዱር እንስሳትን ቁጥር ለመገመት በተወሰነ ጊዜ የሚከናወን ቆጠራ ነው፡፡
5. **"የዱር እንስሳት አደን ኮታ"** ማለት የዱር እንስሳት ቆጠራን መሠረት በማድረግ ከየዱር እንስሳቱ ዝርያ ለአንድ ቁጥጥር አደን ቀበሌ ወይም ክፍት የማደኛ ቦታ በዓመት እንዲታደን የተፈቀደው የዱር እንስሳት ብዛት ነው፡፡
6. **"ስፖርታዊ አደን"** ማለት ለመዝናኛና ለውጤታቸው ሲባል የተለያዩ የዱር እንስሳትን በሕጋዊ መንገድ የማደን ተግባር ነው፡፡
7. **"ፍጆታዊ አጠቃቀም"** ማለት የዱር እንስሳትን ከመኖሪያ ቦታው በመውሰድ ወይም በስፖርታዊ አደን፣ በራንች ወይም ዕርባታ በማሳደግ ለውጤታቸው (ሥጋ፣ ቆዳ፣ ላባ፣ቀንድ፣ጥርስ) ሲባል በመግደል የመጠቀም ስልት ነው፡፡
8. **"የዱር እንስሳት ቁጥጥር አደን ቀበሌ"** ማለት ለዱር እንስሳት ጥበቃ የሚከለልና ቁጥጥር እየተደረገ ሕጋዊ አደን የሚካሄድበት ሥፍራ ነው፡፡
9. "ባለሙያ" ማለት የዱር እንስሳት ቆጠራ የሚያከናውን የመስኩ ባለሙያ ማለት ነው፡፡
10. **"ቡድን"** ማለት የዱር እንስሳት ቆጠራን ለማከናወን ከባለሥልጣኑ እና ከክልሎች የሚመደቡ የመስኩ ባለሙያዎች ቡድን ነው፡፡
11. **"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፤
12. **"ባለስልጣን"** ማለት የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ነው፡፡

13."**ክልል**" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተመለከተውን ማንኛውንም ክልል እና አዲስ አበባንና የድሬዳዋ መስተዳድርን ይጨምራል፡፡

14."**ሰው**" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

15.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. <u>የመመሪያው ዓላማ</u>

1. የዱር እንስሳት ሀብታችንን ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀምና የዱር እንስሳት ሃብቱ ለአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ማድረግ፤
2. የፍጆታዊ የዱር እንስሳት አጠቃቀምንና የዱር እንስሳት ሃብቱን ይዘት በሚመለከት ተገቢውን ክትትል ለማድረግና ሳይንሳዊ የአጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት፤
3. የዱር እንስሳት የአጠቃቀም ሥራን ለማሳለጥ፣ ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት፣ ተጠያቂነትና ወጥነት ያለውን አሰራር ማስፈን፤
4. በአደን ምክንያት በዱር እንስሳት ላይ የሚደርሰውን ተጽዕኖ መቀነስ፡፡

## 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የዱር እንስሳት አደን በሚፈቀድባቸው ቦታዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>ስለ ታዳኝ የዱር እንስሳት ቆጠራ</u>

## 5. <u>ቆጠራ ስለማካሄድ</u>

1. የታዳኝ ዱር እንስሳት ሥነምህዳራዊና ሥነ ህይወታዊ ሁኔታ (ሥርዓተ ተዋልዶ፣ የፆታና ዝርያ ስብጥር፣ የመኖሪያ አካባቢ) በሚመለከት ሳይንሳዊ የዳሰሳ ጥናት ይካሄዳል፡፡
2. የዱር እንስሳቱን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት በማድረግ የተለያዩ የታዳኝ ዱር እንስሳት ቆጠራ ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል፡፡

3. በቆጠራው ወቅት በማደኛ ሥፍራው ውስጥ ያለው ሥነ-ምህዳራዊ መስተጋብር መፋለስ በዱር እንስሣው ቀጣይ ሕልውና ላይ አደጋ የሚያደርስበት ሁኔታ መኖር ያለመኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
4. ቆጠራው በነባር የማደኛ ቦታ የሚከናወን ከሆነ ለጥበቃ ቦታው ተገቢው ሥርዓት አያያዝ የተዘረጋለት መሆኑን መረጋገጥ አለበት፡፡
5. ቆጠራ በሚደረግበት አካባቢ በሠውና በዱር እንስሳት መካከል የተከሠተ ግጭት መኖር ያለመኖሩን መረጋገጥ አለበት፡፡

6. **<u>የታዳኝ የዱር እንስሳት ቆጠራ ቡድን ስለማቋቋም</u>**

1. ለታዳኝ የዱር እንስሳት ቆጠራ ሥራ ከባለሥልጣኑ ሁለት፣ ቆጠራ ከሚከናወንበት ክልል ሁለት በድምሩ አራት አባላቶች ያሉት የባለሙያዎች ቡድን ይቋቋማል፡፡
2. ባለሥልጣኑ የቆጠራ ቡድን መሪውን ይሰይማል፡፡
3. ክልሉ ተወካዮቹን ቆጠራ በሚከናወንበት አካባቢ ከሚገኙ ባለሙያዎች መካከል ይሰይማል፡፡

7. **<u>የቆጠራ ቡድኑ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

1. የቆጠራ ቡድኑ የሥራ ዝርዝር ዕቅድ ያወጣል፤ አስፈላጊውን የሎጅስቲክ አቅርቦትን ያስተባብራል፡፡
2. የሎጂስቲክ አቅርቦቱ እንደ አስፈላጊነቱ በባለሥልጣኑ ወይም በክልሉ ይሸፈናል፡፡
3. በዕቅዱ መሠረት ቆጠራውን ያከናውናል፡፡
4. የቆጠራውን ውጤት ሪፖርት ለባለሥልጣኑና ለሚመለከተው ክልል ያቀርባል፡፡

8. **<u>የታዳኝ ዱር እንስሳት ቆጠራ ስለሚካሄድባቸው ቦታዎች</u>**

1. ነባር የቁጥጥር አደን ቀበሌ ሆኖ ዳር ድንበር ተከልሎ ካርታ ያልተሠራለት ከሆነ ካርታ እንዲሠራለት ይደረጋል፡፡
2. አዲስ ጥያቄ የሚቀርብባቸው የአደን ቀበሌዎች ላይ፡-

   ሀ/ የቆጠራ ቡድኑ የመጀመሪያ ዳሠሳ ጥናት እንዲያከናውን ይደረጋል፡፡

ለ/ ቡድኑ በቦታው በሚያደርገው የዳሠሳ ጥናት መሰረት የቁጥጥር አደን ቀበሌ መስፈርትን ማሟላቱና አለመሟላቱን በማረጋገጥ ሪፖርቱን ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፡፡

ሐ/ የቡድኑ ሪፖርት የተጠናውን ቦታ ዳር ድንበር ከነካርታውና የዱር እንስሳትን ቆጠራ ሪፖርት ያጠቃለለ መሆን አለበት፡፡

## 9. <u>የታዳኝ የዱር እንስሳት ቆጠራ ስልት</u>

1. የታዳኝ ዱር እንስሳት ቆጠራ ቡድን ለቦታው አመቺ ይሆናል ብሎ ያመነበትንና ሣይንሣዊ አግባብነት ያለውን የቆጠራ ስልት ቀይሶ ቆጠራውን ያከናውናል፡፡
2. ከታዳኝ የዱር እንስሳት ቆጠራ ቡድን አራት አባላት መካከል ሦስቱ የሚስማሙበት መረጃ ይሰበሰባል፤ በዚህ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ቡዱኑ ስምምነት ላይ የማይደርስበት ሁኔታ ከተከሰተና በእኩል ድምፅ ከተከፈለ የቡዱን መሪው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
3. የዱር እንስሳውን ኮቴ፣ እዳሪ፣ ድምፅ፣ ጉድጓድ እና የመሣሠሉትን ተዘዋዋሪ መረጃዎችን በመጠቀም የታዳኝ ዱር እንስሳው መኖር ከተረጋገጠ የሌሊት ቆጠራ ይከናወናል፡፡
4. የታዳኝ የዱር እንስሳው ቆጠራ ቡድን ለእያንዳንዱ ዝርያ ተስማሚ የመኖሪያ አካባቢ ለይቶ ቆጠራ ማከናወን አለበት፡፡
5. የታዳኝ የዱር እንስሳው ቆጠራ ቡድን በሥጋ በል የዱር እንስሳት ቆጠራ ተስማሚ መኖሪያን ሲገምት በአካባቢው ከሚኖረው የምግብ አቅርቦት አንፃር መሆን አለበት፡፡
6. ቆጠራው የሚከናወነው ናሙና በመውሠድ ከሆነ የእያንዳንዱ እንስሳ የናሙና ስፋት መጠን ከተስማሚው መኖሪያ አካባቢ መጠን 5% ያነሠ መሆን የለበትም፡፡
7. ከአደን ቀበሌው ጋር በቅርብ ርቀት ብሔራዊ ፓርክ፣ ዱር እንስሳት መጠለያ ወይም ጥብቅ ክልል ካለ በመሀል የ8 ኪ.ሜ. ርቀት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

## 10. <u>የታዳኝ የዱር እንስሳት ቆጠራ ወቅቶች</u>

1. የታዳኝ የዱር እንሣት ቆጠራ በየሦስት ዓመቱ ይከናወናል፡፡
2. የቆጠራውና የአደን መርሀ ግብሮቹ በአንድ ላይ መከናወን የለባቸውም፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት የተቀመጠውዊ የቆጠራ ኘሮግራም እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆነ ከተገኘ ከሦስት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ቆጠራ ሊደረግ ይችላል፡፡

## 11. የታዳኝ ዱር እንስሳት የኮታ አሠጣጥ ስሌት

1. የታዳኝ ዱር እንስሳት ኮታ አሠጣጥ በሀገሪቱ ያለውን የዱር እንስሣት ስብጥርና ብዛት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡
2. የታዳኝ ዱር እንስሳት ቤተሠቦች፣ የበይ ተበይ ግንኙነት፣ አኗኗር፣ ሥርጭት፣ ሥርዓተ-ተዋልዶ፣ ሥነ-ምህዳራዊ ውክልና አንፃራዊ ሥጋት ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተቀመጡትን መሠረት አድርጎ የተሰበሰበውን መረጃ በመተንተን ዓመታዊ ኮታ ይሠጣል፤ የኮታ ስሌቱም ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪ በተያያዘው ሠንጠረዥ ተዘርዝሯል፡፡

## 12. የታዳኝ ዱር እንስሳት ኮታ ስሌት ሪፖርት

የታዳኝ የዱር እንስሳት ቆጠራ ቡድን የኮታውን ስሌት አዘጋጅቶ ሪፖርት በሚያቀርብበት ወቅት የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

ሀ/ ለታዳኝ ዱር እንስሳት በተቀመጠው የመቶኛ ስሌት መሠረት ከተሠራ በኋላ ክፍልፋዩ ከ0.5 በታች ከሆነ ወደ ታችኛው ቁጥር ይጠጋጋል፤ ክፍልፋዩ ከ0.5 እና ከዚያ በላይ ከሆነ ደግሞ ወደ ላይኛው ቁጥር የተጠጋጋ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ለ/ አጠቃላይ የኮታው ስሌት ሲጠናቀቅ ለባለሥልጣኑና ቆጠራው ለተከናወነበት ክልል ሪፖርት መቅረብ አለበት፡፡

ሐ/ ሪፖርቱ ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ባለሙያዎች ቀርቦ ውይይት ከተደረገበትና ከፀደቀ በኋላ ለሚመለከተው የክልል አካልና ለቁጥጥር አደን ቀበሌው ባለይዞታ እንዲያውቁት መላክ አለበት፡፡

## 13. የታዳኝ ዱር እንስሳት ኮታ አጠቃቀም

1. የታዳኝ ዱር እንስሳት ኮታ የሚሰጠውም ሆነ የሚወሰነው በየሶስት ዓመቱ በሚከናወን የታዳኝ ዱር እንስሳት ቆጠራ ውጤት መሠረት ብቻ ነው፤ ከዚህ ውጪ የሚቀርብ ኮታን የመጨመር ወይም የመቀነስ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡
2. ማንኛውም አሳዳኝ ድርጅት የተሰጠውን ኮታ መጠቀም የሚችለው በተፈቀደለት የበጀት ዓመት ብቻ ነው፤ ከዚህ ውጪ የሚቀርብ ማንኛውም ኮታን የመጠቀም ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

3. ማንኛውም አሳዳኝ ድርጅት ባልፀደቀ የታዳኝ ዱር እንስሳት ኮታ ላይ ተመስርቶ የቱሪስት አደን ውል መፈጸምም ሆነ ቅድሚያ ክፍያ መጠየቅ አይችልም፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱትን የአሰራር ሥርዓቶች ለማስፈፀም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 15. ቅሬታዎችን ስለማስተናገድ

1. በዱር እንስሳት ቆጠራና ኮታ አሠጣጥ ምክንያት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በ10 ቀናት ውስጥ ለቡዱኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በቡድኑ መልስ ያልተስማማ ቅሬታ አቅራቢ አቤቱታውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. በባለሥልጣኑ ውሳኔ ያልተስማማ ቅሬታ አቅራቢ አቤቱታውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

### 16. ቅጣት

የዚህን መመሪያ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ወገን በአዋጁና ደንብ እንዲሁም አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 17. ስለተሻሩ ሕጎች

ከዚህ መመሪያ በፊት ወጥተው የነበሩ የዱር እንስሣት ቁጥጥር አደን ቀበሌዎች ይዞታና አጠቃቀም መመሪያዎች ተሽረው በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

### 18. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

### 19. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሰኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## አባሪ 1
## የታዳኝ የዱር እንስሳት የኮታ አሰጣጥ ሰንጠረዥ

| ተ. ቁ. | የዱር እንስሳቱ ቤተሰብ /ዝርያ/ መጠሪያ | የታዳኝ ዱር እንስሳት ብዛት | ዓመታዊ የአደን ኮታ |
|---|---|---|---|
| 1 | ጠጣና ዝንጀሮ (Primates) | >30 | 2.5% |
| 2 | አንበሳ * | >20 | 5% |
| 3 | ሌሎች ሥጋ በል (Carnivores) | >30 | 5% |
| 4 | አዞ | >40 | 2% |
| 5 | ጉማሬ** | >40 | 1% |
| 6 | የደጋ አጋዘን | >40 | 1.5% |
| 7 | የምኒሊክ ድኩላ | >40 | 2% |
| 8 | ልዩ ትኩረት የሚሹ ዕፅዋት በል የዱር እንስሳት (የቆላ አጋዘንና የተራራ ብሆር) | >50 | 2% |
| 9 | ትላልቅ ሣር በል (ጎሽ፣ ሣላ፣ ቆርኬ መጋላ) | >40 | 2% |
| 10 | ሌሎች ዕፅዋት በል የዱር እንስሳት | >40 | 2.5% |
| 11 | ሰጎን | >50 | 2% |

- የአንበሣ ቆጠራ የሚከናወነው የመኖሪያ አካባቢውን እምቅ ህይወታዊ ሀብት ሁኔታ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ሲሆን፤ ከዚህም በመነሳት ሥፍራው ምን ያህል የአንበሳ ቡድን (ኘራይድ) ሊኖርበት እንደሚችል በመገመትና የታዳኝ አንበሣ ቁጥር በመለየት ኮታው ይሰጣል፡፡
- የጉማሬ ቆጠራ የሚከናወነው የአጠቃላይ ቆጠራ ስልትን በመከተል ነው፡፡